# ያለ ምርጫ ተቋም እንዴት ስለ ምርጫ እናወራለን?

ልዑል ሰገድ (ከአቢሲኒያ)
lulethio@yahoo.com

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቦርድ ሰብሳቢን ስለ ምርጫ አንዳንድ መረጃዎች ለመጠየቅ ከቢሯቸው በር ላይ እጠብቃለሁ። አቶ ከማል በድሪ የቦርዱ ሊቀመንበር፣ የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት፣ የህገ-መንግስት አጣሪ ጉባኤ አባልም ናቸው። በተሰጣቸው ሥልጣን ከሳቸው በላይ ስለ ምርጫው ሊጠየቅ የሚገባው የለም ብዬ ነበር የግድ እሳቸውን ለማግኘት ደጅ የጠናሁት።

ሰዓቱ እየገፋ መሔድ ጀመረ። ተስፋ ሳልቆርጥ መጠበቄን ቀጠልኩ። ጸሐፊዎች ቢሯቸውን እየቆለፉ ወጥተዋል። በቦርዱ ካለው ቢሯቸው መግቢያ እኔና በርቀት ፈንጠር ብሎ የቆመው ጠባቂያቸው ብቻ ተፋጠናል። ወደ አቶ ከማል የላኩኝ በቅርቡ “ቦርዱ ነፃ ነው” የሚል ስብከት በአሜሪካ ድምፅ ሲሰጡ የሰማችኋቸው አቶ ተስፋዬ መንገሻ ናቸው።

በአገራችን አቆጣጠር ከምሽቱ 12 ሰዓት ግድም እየሆነ ነው። የቦርዱ ግቢ ጭር ማለት ጀምሯል። ጸሐፊያቸው ሲወጡ ታናግራቸዋለህ ባትለኝና ጠባቂያቸውን ባላይ ኖሮ በዚያ ሰዓት ቢሮ ይኖራሉ ብዬ ባላመንኩ ነበር። ድንገት አንድ መኪና ከውጭ እየተንደረደረች ገብታ የአቶ ከማል ቢሮ ፊት ለፊት ቆመች። በሮች በፍጥነት ተበረገዱ። አቶ በረከት ስምኦን በግራ እጃቸው ወረቀቶች እንደያዙ ሰተት ብለው ገቡ። የቦርዱ ሊቀመንበር ከስራ ሰዓት ውጭ ሲጠብቋቸው የነበሩት አለቃቸውን መሆኑ ገባኝ።በረከት የወያኔ ምርጫ ሀላፊ ሲሆኑ ከማል በድሪ ደግሞ ዛሬም ድረስ ነጻ ነው እየተባለ በወያኔ የሚጮህለት ቦርድ ሊቀመንበር። ሁለቱ ጠባቂዎች የሞቀ የትውውቅ ሰላምታ እንደጨረሱ ፈንጠር በል የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ተሰጠኝ። በኋላ ከቦርዱ አካባቢ ባገኘሁት መረጃ ከስልክ ያለፈ መመሪያ ለቦርዱ ኃላፊዎች የሚሰጥበት የተመረጠ ሰዓት መሆኑን አወቅሁ።

ይሔ የሆነው በ1997 ዓም ሲሆን ዛሬም የዚህ ቦርድ ኃላፊዎች የወያኔ ጉዳይ ፈጻሚዎች መሆናቸውን ልብ ይላሉ። የ1997 ምርጫ ታሪካዊ ነው ከሚሰኝባቸው ምክንያቶች መካከል ለኔ እንደ ምርጫ ቦርድ፣ ፍ/ቤት፣ የመከላከያ፣ የደህንነት እንዲሁም ፓርላማው ምን ያህል ነፃ አለመሆናቸው በወሬ ሳይሆን በተግባር የተረጋገጠበት ወቅት መሆኑ ጭምር ነው። ከዚህ በኋላ ነው ቢያንስ የውጭው ዓለምን ጨምሮ ብዙዎች በጭፍን ተቃዋሚዎችን ምርጫ ግቡ ከማለት አልፈው ተቋማቱ የግድ አስፈላጊዎች መሆናቸውን የተረዱት።

የምርጫ ቦርድ በድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ከምርጫው በፊት የወያኔ እጩዎች ሲመረጡባቸው ያውቃል። ድምፅ ተቆጥሮ ሳያልቅ እነ መለስ ከህግና ሥርዓት ውጭ የሕዝብ ድምፅ ዘርፈው “መንግስት ለመመስረት የሚያበቃ ድምፅ አግኝተናል” ሲሉ ተቀብሎ ያንኑ እንደታዘዘው አድርጓል። የድምፅ መስጫ ኮሮጆዎች ከየወረዳው ዞን ምርጫ ጣቢያዎች እንዳይመጡ፣ ከመጡም እንዳይረከቡ ለኋላፊዎች ከወያኔ መሪዎች የተሰጠው ትዕዛዝ ወደታች የወረደው በእነ አቶ ተስፋዬ፣ በእነ አቶ ከማል በድሪ በኩል ነው።

ሕዝቡ የሰጠው ድምፅ መከበር አለበት ብለው ድምፅ ቆጥረው ማረጋገጫ ፈጥነው የሰጡ አንዳንድ የምርጫ አስፈጻሚዎች መከራ አግኝቷቸዋል። በተቃራኒው የእነ መለስን አፍ እተከተሉ የሕዝቡ ድምፅ ሲሰረቅ አብረው የሰረቁ በምርጫ ማጣራቱ ወቅት ከወያኔ ጎን በመሰለፍ ምርጫ ቦርድ ፍጹም አሻንጉሊት መሆኑን በዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ጭምር ያሳዩ ታማኞች ተሹመዋል ተሸልመዋል። በዚህ ብቃታቸው ለቀጣዩ ምርጫ መታጨታቸው አይቀርም።

የእነ መለስ የአፈና ቡድን የመራጩን የሕዝብ ድምፅ መስረቅ ብቻ ሳይሆን በዝረራ የተሸነፈባቸውን አካባቢዎች ሁሉ ተበቅሏል። ከየአካባቢው የተቃዋሚ ታዛቢውችን፣ የሲቪልማህበራት ታዛቢዎችን፣ የምርጫ ቅስቀሳ አደረጉ ያላቸውን ሁሉ አስሯል ገድሏል። ለአካል ጉዳት የተዳረጉትን ቤቱ ይቁጠራቸው።

ንጹሃን ድምጻችን ይከበር ብለው ስለጮሁ ብቻ በነመለስ ቁጥጥር ስር በተዋቀረው የአጋዚ፣ የፌዴራል ፖሊስ፣ የመከላከያና የክልል ፈጥኖ ደራሾች ደማቸው በከንቱ ፈሷል።ከ197 በላይ ንጹሃንን ያስገደሉት ለፍርድ አልቀረቡም ሌላው ቀርቶ በአንዳንድ አካባቢዎች የታሰሩት ሰዎች ዛሬም አልተፈቱም።

ምርጫ ያለ ነጻ ተቋማት ማለትም ያለ ነጻና ገለልተኛ ምርጫ ቦርድ፣ያለ ነጻና ገለልተኛ የፖሊስ፣ የመከላከያ፣ የደህንነት ተቋማት፣ ያለ ነጻ ፓርላማ፣ያለ ነጻ ፍርድ ቤት እና ያለ ነጻ ሚዲያ ዋጋ እንደሌለው ምርጫ 97 በተግባር አሳይቷል።

በሕዝብ ድምጽ የተዘረፉት የምርጫው አሸናፊዎችን ጭምር ገለዋል።እነ ጁነዲን ሳዶን ያሸነፉት የተቃዋሚ ተመራጭ ስለ ተመረጡ ብቻ ተገለዋል።በሻሸመኔ ዛሬ የፌደራል ፓሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁ የተሸነፈበትን ወረቀት ለመቀየር የኡብኮ ተወካይ የምርጫው ምሽት ቆጠራው ላይ ተገሎዋል። የዚህ አይነት አጋጣሚዎች በርካቶች ናቸው። በየክልሉ መራጮች፣ ህጋዊ የምርጫ ቅስቀሳ አድራጊዎች፣ የተቃዋሚና የሲቪል ማህበራት ታዛቢዎች፣ የተቃዋሚ ተመራጮችና ቤተሰቦች ግንባር ቀደም የገፈቱ ቀማሾች ሆነዋል።

የምርጫው ሰሞን ተቃዋሚዎች በህዝብ የተሰጣቸው ድምፅ ተሰርቆም ፓርላማ መግባት አለባቸው የሚል ጭፍን አመለካከት ነበር። በአገር ውስጥ ግን ፓርላማው የወያኔ አሻንጉሊት መሆኑን ሕዝቡ አሳምሮ ስለሚያውቅ በየ ሕዝባዊ ስብሰባው በደማችን ላይ ተረማምዳችሁ ድምጻችን ተዘርፎ ፓርላማ አትገቡም አለ።

እነ መለስ ለህገ-ወጥ ሥልጣናቸው ህጋዊ ስልጣን ለመስጠት የተወሰኑ ተቃዋሚዎችን እየረገጡም፣ እየደለሉም እያስፈራሩም ወደ ፓርላማ አስገብተዋል። በዋናነት የምርጫው አብላጫ ድምፅ ማግኘቱ ሰፊ ግምት የተሰጠው የቅንጅት መሪዎችን በማሰር ብቻም አልተወሰኑም። ገና ቅንጅት በምርጫው አሸነፈ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ህገ-ወጥ አዋጆችን ፈለፈሉ።

ቅንጅት አዲስ አበባን ይይዛል በማለት የኦሮሞና የአማራን ሕዝብ ለማጣላት በሚል "የኦሮሚያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ነው" አሉ ቅንጅት አልተቃወመም። በ1991 የክልሉን ዋና ከተማ ወደ አዳማ ሲያደርጉ የተቃወሙ በርካታ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ታስረው ተደብድበዋል። ከትምህርት ገበታቸው ተባረዋል። የመጫና ቱለማ መሪዎች ውሳኔው መስተካከል አለበት ስላሉ በሽብር ተከሰው ዛሬም እስር ቤት ናቸው። <<የኦሮሚያ የባህል ማዕከልም ይገነባል፣ ኦሮሚያ ከአዲስ አበባ ሀብት ትጋራለች አሉ።>>ቅንጅት ደገፈው። ድርጅቱ በምርጫ ቅስቀሳው ለከተማዋ ባቡር አስገባለሁ ስላለ ለከተማዋ ባቡር ለማስገባት ፈቃዱ በፌዴራል መሰጠት አለበት የሚል አዋጅ አወጡ። ከዚህ አልፈው የከተማዋን ገቢ ለመቀነስ የመንገድ ትራንስፓርቱን እና ሌሎች አንዳንድ ተቋማትን ወደ ፌዴራል አዞሩ።በዚህም አላበቃ የቅንጅት መሪዎች መካከል ብዙዎቹ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ናቸው በሚል <<ተቃዋሚዎች በፓርላማ በኢኮኖሚ ጉዳይ አጀንዳ ማሲያዝ አይችሉም>> የሚልም ህገ ወጥ ህግ አወጡ።

በአደባባይ የሕዝብ ደምፅ ከመዝረፍ ጀምሮ እስከ ንፁሃን ጭፍጨፋ፣ የቅንጅቱን መሪዎች ከማሰር አልፎ ድርጅቱን አፍርሶ ስያሜውን ለፈለገው ቡድን እስከመስጠት ሔዷል። በእነዚያ ሒደቶች ሁሉ የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎች መለስ እና በረከት የሚሰጣቸውን የጽሑፍና የቃል ትዕዛዝ ሁሉ ሲያስተጋቡ የነበሩ ናቸው።

ተቃዋሚዎች ለምን ፓርላማ አልገቡም እያሉ ሲራገሙ የነበሩ የተቃዎሚዎች ፓርላማ መግባት ውጤት አለማምጣቱን በተግባር አይተውታል። የአገሪቱን ባንዲራ ያውለበለበ ይቀጣል ከሚል አዋጅ አንስቶ የዜጎችን ሰብዓዊ መብት የሚጻረር አሸባሪ ህግ በፀረ አሸባሪነት ስም እስከማውጣት ሔደዋል።በህገ መንግሥቱ የተፈቀዱ የንግግር መብቶች ተገድበዋል።ባለፈው ምርጫ ጉልህ የገለልተኛ ሚና የነበራቸው ብዙዎቹ መንግስታዊ አልሆኑ ድርጅቶች በአዋጅና በቀላጤ እንዲዳከሙ ተደርገዋል።በምትካቸው የወያኔን ድምጽ ብቻ ሚናገሩት እንዲኖሩ እተደረገ ነው። ፓርላማውን ጨምሮ ያለ ነፃ ተቋማት በምርጫ ተመርጦ ድምፅ ተከብሮ፣ በድምፅም መንግስት መመስረት የሚቻልበት ሁኔታ እስከሌለ ምርጫ ማጭበርበሪያ መሆኑ ዛሬ ለመላው አገሪቱ ሕዝብ ግልፅ ሆኗል።

እነ መለስ የግድ ምርጫ ማድረግ ይፈልጋሉ። ለህገ ወጥ ዘረኛ ሥርዓታቸው የሌለ ህጋዊ መልክ ለመቀባት ያላቸው ብቸኛ አማራጭ አድርገውታል። ከምርጫ 97 በኋላ የበለጠ የአፈና መዋቅራቸውን አጠናክረዋል። በአገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን ያሉ ተቃዋሚዎች መንቀሳቀስ አልቻሉም።አገር ያወቀውን ሀቅ ተናገርሽ ብለው ብርቱካንን ያሰሩት ያው ገና ለገና ፓርቲው ጠንክሮ ይወጣል በሚል ነው።ያልታሰሩትም በቁም እስር ላይ ናቸው።ሕዝቡን ማደራጀት አልተፈቀደላቸውም። አባሎቻቸው እየተደበደቡ፣ በፈጠራ ክስ እየታሰሩ ነው።

የወያኔ መሪዎች ከምርጫ 97 በኋላ ሠራዊቱን፣ ደህንነቱን፣ የፌደራል ፖሊስን፣ የአዲስ አበባ ፖሊስን እና እንደ አግአዚ ያሉ ልዩ ጦሮችን በአንድ የትግራይ ብሄር አባላት የበላይ አመራር ሥር አዋቅረዋል። ፍርድ ቤቶች ከመቼውም ጊዜ በላይ በዜጎች መብት የወያኔ መሪዎች የሚቀልዱባቸው ተቋማት ሆነዋል።የአገሪቱን ሕዝብ ሊያገለግል የሚገባው መገናኛ ብዙሃን ዛሬም የገገሮቹ የፕሮፓጋንዳ ማሽን ነው። ነጻ አስተያየት ብሎ ነገር የለም። የህዝቡ ድምጽ አይሰማም። ታዲያ በዚህ ሁኔታ እንዴት ዓይነት ምርጫ ማድረግ ይቻላል?

የአሻንጉሊቱ ምርጫ ቦርድ አሻንጉሊት መሪዎች ዛሬ በአደባባይ ብቅ ብለው ስለ ምርጫ ቦርድ ገለልተኝነት ሊነግሩን ሲሞክሩ ያሳፍራል፡፡ጭራስ ይግረማችሁ ብለው ምርጫ ያጭበረበረን እንቀጣለን ብለው እስከመሳለቅ ደርሰዋል።ምርጫ ያጭበረበረ የሚቀጣበት ነጻ ሥርዓት በኢትዮጵያ ቢኖር ኖሮ እነ መለስና የምርጫ ቦርዱ ሰዎች ወህኒ በወረዱ ነበር።ይህንን ቦርድ ሕዝቡ በወሬ ሳይሆን በተግባር የወያኔ መጫወቻ ተቋም መሆኑን በቅርብ ተመልክቷል።

ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ያለ ነፃ ተቋማት ምርጫ ማድረግ ጥቅሙ ለወያኔ መሪዎች ብቻ ነው። ሕዝቡን አስፈራርተው ለምርጫ ካልወጣችሁ የማዳበሪያ እህል የለም፣ እናስራችኋለን፣ እንደእነ እከሌ እንገድላችኋለን ማለታቸው አይቀርም። ይሔ የሚጠበቅና ከአሁኑ የተያዘ ዘመቻ ነው።

በአገራችን በነፃ መደራጀት፣ መሰብሰብ፣ ሃሳብን በነፃ መግለጽ የለም። የአፈና ሥርዓቱን የበለጠ ለማጠናከር የግንቦት 1997 ምርጫን ታሳቢ አድርጎ የወጣው እና ሥራ አጥን ሁሉ ወንጀለኛ የሚያደርገው የአደገኛ ቦዘኔ አዋጅ ዛሬ ፀረ ሽብር የሚል ህግ ተጨምሯል፡፡ ወያኔ በምርጫ ዋዜማ አፈናውን ለማጠናከር የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ የታወቀ ነው።

አንዳንዶች ዛሬዋ ኢትዮጵያ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ  ሰላማዊ በሆነ መንገድ መታገል ይቻላል ሲሉ እንጂ የሚቻለውን ሰላማዊ ትግል ሲመሩ አልታየም። ሕዝቡም በምርጫ 97 ሰላማዊ ትግል ለማካሔድ የተዘጋጀና ይህንንም በተግባር ያረጋገጠ ነው። በሥልጣን ላይ ያለው የአፈና ቡድን ግን ለዜጎች ሰላማዊ እንቅስቃሴ በጥይት አረር ምላሽ ሰጥቷል። ይሔ ባላንጣ ባለበት እንዴት ያለ ሰላማዊ ትግል እንደሚደረግ በዚህ መሰሉ ሂደት የሚደረግ ምርጫ ምንስ ውጤት እንደሚገኝበት ቢገልጹልን መልካም ነበር።

አንዳንድ በአገር ውስጥ ያሉ ተቃዋሚዎች በልደቱ (ክህደቱ) የሚመራውን ኢዴአፓን ጨምሮ ሳይጠሩ ሮጠው ወደ ምርጫ ገባን የሚሉትን ያህል ምርጫ ቦርድ ገንዘብ ይሰጣል ሲባል ያንን ገንዘብ ለመውሰድ ብቻ “ፓርቲ” የሚያቋቁሙ ሊኖሩ ይችላሉ። አንዳንዶች እንደ እነ ኦቦኮ የሉ “ፓርቲህን ከምናፈርሰው ፓርላማ ከምትገባ” ሲባሉ ሮጠው ፓርላማ በመግባት “ልባቸው” ስለታየ ዛሬም ወደ ምርጫ ግባ የሚል ተጽዕኖ ሊደግባቸውና ለዚያ ሊንበረከኩ  ይችላሉ። የቀሩትም ተቃዋሚዎች የወያኔ መሪዎች ከምርጫው እንዳያፈገፍጉ የተለያዩ ዘመቻዎች ያደርጉባቸዋል፡፡ ዓላማው ምርጫ የተባለ ቴአትር ለመስራት ስለሆነ በዚህ የተጋባዥ ተዋንያን ካባ ለብሰው መገኘት ብቻ ነው።ይህ ሁሉ መሆኑ ግን በአገራችን ምርጫ ተደረገ አያሰኝም። ይሄ ምርጫ አይደለም።

የወያኔ መሪዎች አስቀድመው ኮሮጆ ቢሞሉ እንደ ምርጫ 97 ሰፊ ሕዝባዊ ተቃውሞ እንደማይጠብቃቸው ያውቃሉ። ሕዝቡ ያለ ነፃ ተቋማት የሰጠው ድምፅ እንደማይከበር አውቋል። መምረጥ እፈልጋለሁ የምመርጠው ግን ዲሞክራሲያዊ ተቋማት ሲመሰረቱ፣ ነፃ ምርጫ እንጂ በማጭበርበር ለተሞላ ምርጫ አጃቢ አልሆንም ካለ ቆይቷል።

የኢትዮጵያ ሕዝብም ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ያስፈልገዋል። የዚህ አይነቱ ምርጫ ቢኖር ኖሮ ዛሬ ከምርጫ 97 ግንባር ቀደም ተሳታፊዎች መካከል በርካቶች አዲስ መንገድ ባልመረጡ ነበር። የሕግ የበላይነት የማይከበርበት ሀገር የሚደረግ ምርጫ የሕዝብ ድምፅ የሚከበርበት ሳይሆን በሕዝቡ ስም ጨቋኞች የስልጣን ዕድሜያቸውን ማራዘሚያ እንደሚያደርጉት ደጋግመን በአገራችን ተመልክተናል።

ከየትኛውም አቅጣጫ ይሁን ተቃዋሚዎችን ወደ ምርጫ ግቡ ማለት ፍትሐዊ አይደለም። የሕዝብ ድምፅ ሰርቆ በህገ-ወጥ ስልጣን ሙጥኝ ያለው አምባገነናዊ ሥርዓት የገደላቸውን ሰማዕታት መስዋዕትነት ዋጋ ማሳጣት፣ እነዚያ ንጹሃን ላይ የተፈጸመውን ግፍ መርሳት ነው።

የምርጫ ቦርድ ትላንትም ሆነ ዛሬ ወያኔ እስካለ ነፃ ሊሆን አይችልም። ነፃ የምርጫ አስፈጻሚዎችም አይመደቡለትም። ይህንን የተገነዘበ ሁሉ ነፃ የምርጫ ሥርዓት፣ ነፃ ተቋማት እስኪመሰረቱ ድረስ የዚህ ሥርዓትም ምስረታ በሕዝቡ የጋራ ትግል እውን እስኪሆን የወያኔ መሪዎች ባዘጋጁት የይስሙላ ምርጫ መሳተፍ አይገባም።

በዚህ ምርጫ መሳተፍ ለማንኛውም ሕዝባዊ ወገንተኝነት አለኝ ለሚል ተቃዋሚ ፓርቲ ትልቅ ፈተና ነው። ይሔ የማያልፉት ፈተና ላይ ከመድረሳቸው በፊት እያንዳንዱን ነገር በጽሞና መመርመር ይገባቸዋል። ድምፅ የሚዘረፍበት፣ በተፈለገው ደረጃ ከሚጭበረበርበት የምርጫ ሥርዓት ምን ትርፍ ይገኛል ብለው እንደሚጠብቁ ለሕዝቡ የማስረዳት ግዴታ አለባቸው። ካልሆነ ግን በሕዝብ የመተፋትና ከጠላት ጋር እንደማበር ተደርጎባቸው ሊቆጠር ይችላል።

በአገራችን ላይ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመጣ የሚፈልግ ማንኛውም በአገር ውስጥ ይሁን በውጭ ያለ ወገን የሚያደርገውም እንቅስቃሴ ወደ እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የሚወስዱት ነፃ ተቋማት የሚመሰረትበትን ሥርዓት ለመመስረት የሚደረገውን ትግል መደገፍ ነው።

ዛሬ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስረዳው ፍጹም ያፈና ሥርዓት መንገሱን እንጂ ምርጫ የሚደረግበት ነጻ የውድድር ሜዳ አለመኖሩን ነው። ስለዚህም ነው ከዚህ ቀደም እንደነበረው ሕዝቡ እየተገደለ፣ እየታሰረና እየተገረፈ በድፍኑ ወደ ምርጫ ግቡ የሚል ድፍን አስተያየት አድማጭ ከማግኘት ይልቅ ለትዝብት የሚጥል ድምዳሜ የሚሆነው።

የእነ መለስ አስተዳደር የምርጫ ቦርድ ኃላፊዎችን እንደ ግል ሬዲዩ በፈለጉት ሰዓት እየከፈቱ የመሰላቸውን ሊያስለፈልፏቸው ይችላል። የቦርዱ በየትኛውም ደረጃ ያለ ኃላፊ ያለውን የይስሙላ ስልጣን የማያውቅ የለም። ከላይ ዝቅ ሲባልም ገለልተኛ ሊሆኑ ቀርቶ ከጥቂት ዓመታት በፊት በግልፅ የወያኔ አባላት መሆናቸው የሚታወቁ ግለሰቦች ጭምር ነው።

በቀጣዩ ዓመት የሚደረገው የይስሙላ ምርጫ ሊያሳስበን አይገባም።ውጤቱ አስቀድሞ የታወቀ ነው።ወያኔ ራሱ አስመራጭ፡ ምርጫ ተወዳዳሪ፡ ድምጽ ቆጣሪ፣ ቅሬታ ሰሚ ነው።ስለዚህ ሳይወዳደር ህዝብ ሳይመርጠው አሸንፏል። ሊያሳስበን የሚገባው እንዴት ባለ ፍጥነት እውነተኛ የምርጫ ሥርዓት በአገራችን ይመሰረታል ?ብለን ራሳችንን መጠየቅ ብሎም ወደዚያ ጎዳና የሚወስደውን ሁሉን አቀፍ ትግል ማድረግ ነው።

ከዚያ ውጭ በይስሙላ ምርጫ መሳተፍ በምንም መንገድ የዴሞክራሲ ሒደትን አያመጣም።አያዳብርም።በተጭበረበረ ምርጫ የዳበረ ዲሞክራሲ የለም። የብዙ የተጭበረበሩ ምርጫ ውጤቶችም አንድ ዕውነተኛ ምርጫ አይወልድም።